# ቅንን አስቡ!
# እውነትን ተናገሩ!
# መልካምንም አድርጉ!
## እግዚአብሔርን መምሰል ይህ ነውና።

# Think Right!
# Speak The Truth!
# Do Good!
# This Is The Image of God.

ይህ ዘይቤ፡ የእውነተኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የሕይወታቸው መርኆ ነው።

አዎን! ይህ ዘይቤ፡ ሙታን፡ "ይህ ዓለምና መጪው ዓለም" እያሉ፡ ዛሬ በሚገኙበት፡ በዚህ ዓለምና ገና፡ በተስፋ በሚጠብቁት ዓለም፡ እውነተኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የ፯ሺ፭፻፮ (የሰባት ሺህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት ዕድሜ ባላት፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ተመሥርተውና ቆመው፡ ይኸው አኹን፡ በነፍሳዊው፥ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው የሰውነት ኹለንተናቸው የሚኖሩበትና ይህንኑ ህልውናቸውን እያካኼዱ የሚቀጥሉበት፡ የትንሣኤና የሰንበት ዘለዓለማዊ ሕይወታቸው፡ በአጭር የተገለጸበት ቃል ነው።

አዎን! በእርግጥም፡ ይህ ዘይቤ፡ እውነተኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በአንድ በኩል፡ ፈጣሪያቸውና አምላካቸው፥ አባታቸውና መድኃኒታቸው፥ ካህናቸውና ንጉሣቸው በኾነው፡ በእግዚአብሔር ወልድ መሢሕ ኢየሱስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ሃይማኖታቸውና አገራቸው፥ እናታቸውና ቤዛቸው፥ ክህነታቸውና ንግሥታቸው በኾነችው፡ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነትና ንግሥተ ንግሥታትነት በምትመራው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታቸው እየተዳደሩና እየኖሩ ያሉበት ሕይወታቸው ነው።

ይህ ዘይቤ፡ በበለጠ እንዲብራራ ካስፈለገ፡ እንዲህ በሚል ምጥን ዐረፍተ ነገር፡ ሊቀርብ ይችላል፡- እውነተኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ከመንፈስ ቅዱስ ባገኙትና አምነው በተቀበሉት የህልውና ሥርዓታቸው፥ በሚፈጽሙትም የኑሮ ምግባራቸው፡ በመጀመሪያ፡ የእግዚአብሔር የኾኑትን፡ ቀናውንና እውነቱን፥ መልካሙንም ኹሉ፡ የዲያብሎስ ከኾኑት፡ ከጠማማው፥ ከሓሰቱና ከክፉው፡ ለይተው ማወቅን ያስቀድማሉ። ቀጥለው፡ ጠማማውን፥ ሓሰቱንና ክፉውን ትተው፡ ቀናውን፥ እውነቱንና መልካሙን መምረጥን ያስከትላሉ።፥ በመጨረሻ፡ ጠማማውን፥ ሓሰቱንና ክፉውን አስወግደው፡ ቀናውን፥ እውነቱንና መልካሙን በማድረግ ይደመድማሉ።